በድረ ገፃችን ላይ ይገኛል
http://www.ethiopian-bar.org/

# ተ ሚ ጋ ች

ሰኔ 30 ቀን 2009ዓ.ም. ቅፅ ፩ ፤ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ በየ፪ ወራት የሚታተም።

## ኢሕባማ የጠበቆች የሥነምግባር ደንብ አፈፃፀም ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ የግማሽ ቀን ውይይት አዘጋጀ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር “የጠበቆች የሥነምግባር ደንብ አፈፃፀም ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች” በሚል ርዕሰ-ጉዳይ በኪንግስ ሆቴል ግንቦት 26 ቀን 2009 ዓ.ም. ውይይት አካሂዷል። በዚህ የግማሽ ቀን ወይይት ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፌደራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ፈቃዱ ደምሴ እና የቀድሞ የማኅበሩ ምክትል ፕሬዝዳንት እና የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑት አቶ አበበ አሣመረ በፅሁፍ አቅራቢነት የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑት አቶ በሻዳ ገመቹ በአወያይነት መሳተፋቸውን ቁጥራቸው ወደ 70 የሚጠጉ የሕግ ባለሙያዎች በአውደጥናቱ ላይ መገኘታቸው ታውቋል። በዚህ የግማሽ ቀን የውይይት መድረክ ላይ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክትና የውይይቱን በይፋ መከፈት አብስረዋል።

በውይይቱ ላይ የጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ አፈፃፀም ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ያተኮሩ ሁለት ፅሁፎች የቀረቡ ሲሆን አቶ ፈቃዱ ደምሴ የሥነ ምግባር ፅንሰ ሃሳብና ምንነትን፣ የሥነ ምግባር ምንጮችንና የሥነ ምግባር መርሆዎችን የፌደራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሙያ ሥነ ምግባር ምንነትና ጠቀሜታዎቹን ፤ የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር ሥራዎች ለመስራት ያሉ አስቻይ መልካም አጋጣሚዎችን፣ ውስንነቶችን፣ በጠበቆች በኩል የሚፈፀሙ የሥነ ምግባር ግድፈትና ችግሮችን፣ ደንበኞች በጠበቆች ላይ ያሏቸውን አስተያየትና ምልከታ፣ ጠበቆች እራሳቸው የሚያነሷቸው ችግሮች፣ ጠበቆች ሊላበሷቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦችን በመለየትና ለችግሮቹ የመፍትሔ ሃሳቦችን በማብራራት ገለፃቸውን አጠቃለዋል።

ሌላው የዕለቱ የመወያያ ጽሁፍ አቅራቢ የሆኑት አቶ አበበ አሣመረ ፅሁፋቸው ቀደም ሲል የጠበቆች የሥነ ምግባር ችግርን በተመለከተ ለትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ የቀረበ እንደነበር እና በዕለቱ የሚያቀርቡት ፅሁፍም ከዚሁ ጥናት ላይ ተወስዶ ለዚህ መድረክ እንዲመጥን ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ለተሳታፊው አስገንዝበዋል። ማብራሪያቸውን በመቀጠል ሕግና የሕክምና ሙያ እጅግ ረዘም ያለ ጊዜን ያስቆጠሩ የሥነ ምግባር መርሆዎች ያሏቸው ሙያዎች መሆናቸውን ያስታወሱት አቶ አበበ ጥብቅና ፍትህ ማግኘት ለሚባለው ለሰዎች መሠረታዊ መብት መረጋገጥ አዎንታዊ አስተዋፅዖ የሚያበረክት የሙያ ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን ከፍ ባለ የሞራል ደረጃ እና ግብረገባዊ በሆነ አኳኋን ሙያውን ተግባራዊ ማድረግ እንደ-ሚያስፈልግ አበክረው ገልጸዋል። አያይዘውም ከተለያዩ አካላት በሰበሰቧቸው መረጃዎች መሠረት አንድ አንድ ጠበቆች ሙያው ከሚጠይቀው ሥነምግባር ውጭ

(ወደ ገፅ 5 የዞረ)

## ኢሕባማ ነፃ የሕግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን በአሳይታ እና በጋምቤላ ከፈተ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በኢትዮጵያ መንግስትና በአውሮፓ ኅብረት በሚካሄደው ሁለተኛው ዙር የሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ 2 ፕሮግራም ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አሳይኢታ ከተማ እና በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጋምቤላ ከተማ ሁለት የነፃ የሕግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ማቋቋሙ ታወቀ።

ኢሕባማ በአፋር ክልል አይሳኢታ ወረዳ ፍርድ ቤት ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለማዕከሉ የሚሆን ቢሮ በነፃ

(ወደ ገፅ 7 የዞረ)

### በዚህ ዕትም

⇒ የማኅበሩ መልዕክት 1
⇒ ዜና 2
⇒ ከጠበቃ ማርቆስ ወልደሰንበት ጋር ....ቃለ መጠይቅ 4
⇒ ስለአዲሱ የንግድ ምዝገባና 6
⇒ ልዩ ልዩ መረጃ 8

## የኢትዮጵያ ሕግ ባለሞያዎች ማኅበር መልዕክት

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያዎች ማሕበር በሀገራችን ውስጥ ካሉ የሙያ ማሕበራት መካከል በአንጋፋነቱ ግንባር ቀደም ሲሆን በቅርቡም የ50ኛዓመት በዓሉን በደመቀ ሁኔታ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች አክብሯል:: በእነዚህ ዓመታት ማሕበራችን ሁኔታዎች በፈቀዱት መጠን የተለያዩ ሥራዎችን አከናውኗል:: እያከናወነም ይገኛል::

በዚህ ረገድ ለማህበራችን አባላት እየተሰጡ የሚገኙት ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠናዎች፣ ለማህበረሰቡ የተመቻቹት የነጻ የሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎቶች፣ በተሚጋች እና በኢትዮጵያ ጠበቆች መጽሔት እየተሰራጩ የሚገኙት የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሑፎችና የምርምር ሥራዎች በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ናቸው:: ከዚህ በተጓዳኝ ማሕበሩ የፓን-አፍሪካ ጠበቆች ማሕበርን በመመሥረት ረገድ ያለው እጅግ የላቀ ሚና እና ከዓለም ዓቀፍ የጠበቆች ማሕበር አባል መሆኑና ያለው ጥብቅ የሥራ ቁርኝት የማሕበራችንን ዓለምዓቀፋዊ ተቀባይነት ማሳያ ናቸው::

ይህ የማሕበሩ አገልግሎት ግን በአባላት ውስንነት ምክንያት ሁሉንም የሕግ ባለሙያ ጠቅሟል ለማለት አያስደፍርም:: የሕግ ባለሙያዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ካላቸው ስፍራ አንጻር እና በእውቀትም ሆነ በገንዘብ የሚያደርጉት አስተዋጽዎ ከፍተኛ ነው:: ሙያው ለሌሎች ችግር መድረስን እና መጨነቅን የሚጠይቅ በመሆኑ የሕግ ባለሙያዎች ከዚህ አንጻር ብዙ ይጠበቅብናል:: ማኅበሩ የቆመላቸውን እሴቶች በተለይም የሕግ የበላይነት መከበር እና የፍትህ ተደራሽነትን እውን ለማድረግ የሕግ ባለሙያዎች አቅማቸው የፈቀደውን አስተዋፅዎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ማኅበራችን ለነዚህ እሴቶች የቆመ በመሆኑ ተገቢውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ተገቢው መድረክ ነው ብለን እናምናለን:: በመሆኑም በዚህ አጋጣሚ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የማሕበራችን አባላትና ተባባሪ አባላት እስከአሁን ላደረጉት አስተዋጽዎና ድጋፍ ምስጋናችን እያቀረብን የማሕበሩ አባላት ያልሆኑና በተለያየ ኃላፊነት ላይ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች የማሕበሩ አባል፤ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ የሕግ ተማሪዎች ደግሞ ተባባሪ አባል በመሆን ለሀገራችን የሕግ ሥርዓት መጎልበት የበኩላችንን አዎንታዊ አስተዋፅኦ በጋራ ማበርከት እንችል ዘንድ በማሕበሩ የሥራ አሥፈፃሚ ኮሚቴ ሥም ጥሪዬን አቀርባለሁ::

ቴዎድሮስ ምህረት
የማሕበሩ ሊቀመንበር

**ማስታወሻ**

የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ ታምራት ኪ/ማርያም ከጥር 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በአቶ ቴዎድሮስ ምህረት መተካታቸውን ለአንባቢያን እንገልጻለን።

## ኢሕባማ በውጭ ሀገር የተሰጡ የግልግል ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ሕግ ያላቸው ተቀባይነትና ተፈፃሚነት ላይ የግማሽ ቀን ውይይት አካሄደ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር(ኢሕባማ) “በውጭ ሀገር የተሰጡ የግልግል ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ሕግ ያላቸው ተቀባይነትና ተፈፃሚነት” በሚል ጭብጥ ላይ ያተኮረ የግማሽ ቀን ውይይት መስከረም 28/2009 ዓ.ም. ከ 2፡30- 7፡00 በራስ ሆቴል የሀገር ባሕል አዳራሽ ማካሄዱ ታወቀ። ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ጽሁፍ ያቀረቡት በመስኩ በሕግ 2ኛ ዲግሪ ያላቸው፤ የሕግ አማካሪና ጠበቃ አቶ ሚካዔል ተሾመ ሲሆኑ በሃሳብ ሰጭነት በውይይቱ ላይ የተካፈሉት ወ/ሪት ልዩ ታምሩ የአፍሪካ የዓለም አቀፍ የግልግል ዳታቤዝ (I - Arb Africa) መሥራችና ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ ረዳት ፕሮፌሰር ፍቃዱ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግና የሀገር አስተዳደር ኮሌጅ መምህር እና የሕግ አማካሪና ጠበቃ በአወያይነት መሳተፋቸው ታውቋል። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም ባደርጉት የመክፍቻ ንግግር ለጽሁፍ አቅራቢው ለአቶ ሚካዔል ተሾመ፤ ለሃሳብ ሰጭዋ ወ/ሪት ልዩ ታምሩ እንዲሁም ለአወያዩ ረዳት ፕሮፌሰር ፈቃዱ ጴጥሮስ ላሰዩት በጎፍቃደኝነት አመሰግነው በተለይ ረዳት ፕሮፌሰር ፈቃዱ ጴጥሮስ እንደ አምና ሁሉ በዚህ ውይይት ላይ በመገኘት የምንጊዜም አጋርነታቸውን አረጋግጠውልናል” በማለት አድናቆታቸውን ገልጸዋል። በዚሁ ንግግራቸው አቶ ታምራት በዚህ ዓመት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በተለይም በግልግል ዳኝነት፣ በግንባታ ሕግ፣ በንግድ ምልክት ሕግ እንዲሁም በቅጂና ተዛማጅ ሕጎች ዙሪያ ማኅበሩ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ዕቅድ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ለተሳታፊዎች ይፋ አድረገዋል። በዕለቱ ወይይት ላይ 40 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።

## በባለአክሲዮን ውክልና የመሳተፍ መብት አድማስ የተካሄደ ውይይት

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር “በንግድ ሕጉ መሠረት በባለአክሲዮን ውክልና የመሳተፍ መብት አድማስ ወይም “ Exercising Proxy Right under the Commercial Code” በሚል ርእስ ጥቅምት 26 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 7፡00 በዋቢ ሸበሌ ሆቴል የግማሽ ቀን ትምህርታዊ ውይይት አካሄዷል። በአቶ ኃይሉ ቡራዩ/ጠበቃና የሕግ አማካሪ/ ፅሑፍ አቀራቢነት እና በአቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ የቀድሞ ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ የቦርድ ሊቀመንበርና የሕግ አማካሪና ጠበቃ አወያይነት የተካሄደውን ይህን የግማሽ ቀን ትምህርታዊ ውይይት በእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት የከፈቱት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚደንት አቶ ታምራት ኪዳነማሪያም ሲሆኑ ፕሬዚዳንቱ በዚህ ንግግራችው የእለቱ ውይይቱ የተዘጋጀው በማህበሩ የተከታታይ የሕግ ትምህርት ቋሚ ኮሚቴ መሆኑንና ኮሚቴው ከያዛቸው ተከታታይ የሕግ ትምህርት እቅዶች መካካል በባለአክሲዮን ውክልና የመሳተፍ መብት አድማስ ላይ የሚደረገው የእለቱ ውይይት አንዱ መሆኑን አስታውሰው ማህበሩ ወደፊት በንግድ ሕጉ ዙሪያ ሰፊ ሥራ ለመስራት ማቀዱን ለተሳታፊዎች ገልጸዋል። ከግል እና የመንግሥት ባንኮች፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከፌደራል ፍ/ቤቶች፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች፣ ከጠቅላይ ዐ/ሕግ፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ከማህበሩ አባላትና የሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ 57 ባለሙያዎች በውይይቱ መሳተፋቸው ታውቋል።

## የኮንስትራክሽን ሕግን ዋና ዋና ገፅታዎች የሚዳስስ ዓውደ ጥናት ተካሄደ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር **“የኮንስትራክሽን ሕግ/ውል ዋና ዋና ገፅታዎች”**” በሚል ርእስ ታኅሳስ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ቀኑ 6፡30 በሰሜን ሆቴል የግማሽ ቀን ትምህርታዊ ውይይት አካሄዷል። በአቶ ፋሲል ታደሠ የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር ጽሑፍ አቅራቢነት በመስኩ የረዥም ጊዜ ልምድ ባላቸው እና የሕግ አማካሪና ጠበቃ በሆኑት በአቶ ዜና ደባሱ አወያይነት የተካሄደውን የግማሽ ቀን ወይይት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በዚሁ ንግግራቸው ውይይቱን ያዘጋጁት የማኅበሩ የኮንስትራክሽን ሕግ ኮሚቴ ከተከታታይ የሕግ ትምህርት ኮሚቴ ጋር በመተባበር መሆኑን ጠቅሰው ጽሁፍ አቅራቢውን አቶ ፋሲል ታደሠን እና አወያዩን አቶ ዜና ደባሱን በትምህርታዊው ውይይት ላይ በመገኘት በመስኩ ያላቸውን እውቀትና ልምድ ለማካፈል ፈቃደኛ ሆነው በመምጣታቸው እንዲሁም ተሳታፊዎች የማህበሩን ግብዣ ተቀብለው በውይይቱ ላይ ለመሳተፍ በመምጣታቸው አመስግነዋል። ከማህበሩ አባለት እና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች፤ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከተሰማሩ ድርጅቶች እና ማህበራቶች የተውጣጡ 74 ተሳታፊዎች በውይይቱ ላይ መገኘታቸው ታውቋል።

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር እና የኢትዮጵያ ወጣት የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የ30 ደቂቃ የሬዲዮ ፕሮግራም ጀመረ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከሶሎሞን አድቨርት ኤንድ ፐብሊኬሽን ጋር ለ25 ተከታታይ ሳምንታት በኤፍ ኤም አዲስ 97.1 “የኔ መንገድ“ በሚለው የሬዲዮ ፕሮግራም አማካኝነት በፍትህ ተደራሽነት እና ሌሎች ሕግ ነክ ጉዳዮች ላይ ዘወትር ሃሙስ ከምሽቱ 3፡00-3፡30 የ30 ደቂቃ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀትና ለማስራጨት በገባው ውል መሰረት ፕሮግራሙ ከሚያዚያ 19 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ መሰራጨት መጀመሩ ታወቀ። ፕሮግራሙ በገንዘብ የሚደ-ግፈው የአውሮፓ ሕብረት ሲሆን ይህ ዜና እሰከ-ሚዘጋጅበት እለት ድረስ በተለያዩ የሕግ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች በአየር ላይ መዋላቸው የታወቀ ሲሆን ስርጭቱ በመጪዎቹ ወራቶችም እንደሚቀጥል ከማኅበሩ ጽ/ቤት የወጣው መረጃ ያመለክታል።

## በኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ሕግ እና የኮፒራይት የጋራ አስተዳደር ማኅበራት አመሠራረትና አሠራር ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሄደ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር "የኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ሕግ ቅኝት" በቀድሞ የኢሕባማ ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም /የሕግ አማካሪና ጠበቃ/፤ "የኮፒራይት የጋራ አስተዳደር ማኅበራት አመሠራረ አሠራር በንጽጽር የቀረበ ጥናት" በወ/ት ሰብለ ገብረጊዮርጊስ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ/ እንዲሁም፤ "የቅጂና ተዛማች መብቶች ማሻሻያ አዋጅ ላይ የቀረበ ጥናት" በአቶ ወሰን ሙሉ / በአዕምሯዊ ንብረት ኤጀንሲ በኮፒራይት ዳይሬክቶሬት የቅጂ መብት ሕጋዊ ተፈጻሚነት ቡድን መሪ/፤ ታህሣሥ 15 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡30 እስከ ቀኑ 9፡00 በአዕምሯዊ ንብረት ኤጀንሲ አዳራሽ የአንድ ቀን ትምህርታዊ ውይይት ማኪሄዱ ታውቋል፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት የመወያያ ጽሁፎች ላይ የተካሄደውን ውይይት የመሩት አቶ ደረጀ ወርቁ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ/ ሲሆኑ የቅጂና ተዛማች መብቶች ማሻሻያ አዋጅ ላይ በቀረበው ጽሁፍ ላይ የተካሄደውን ውይይት የመሩት አቶ ዘላለም ጌታሁን /የሕግ አማካሪና ጠበቃ/ መሆናቸው ታውቋል፡፡ 76 የሚሆኑ የማኅበሩ አባላት፣ ከሕግ አማካሪዎችና ጠበቆች፣ ከመንግሥት ሠራተኞች፣ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወካዮች፣ ከአርት ሙያ ማኅበራት ተወካዮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት ይህን ውይይት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸው የከፈቱት የማህበሩ ፕሬዚዳንት እና የእለቱ ጽሁፍ አቅራቢ አቶ ታምራት ኪዳነማርያም ዐውደጥናቱ እንዲዘጋጅ ወጪውን ከመሸፈን አልፎ ጥናታዊ ፅሁፍም በማቅረብ አስተዋጽዖ ላደረገው ለአእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የላቀ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ አያይዘውም የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር የአእምሯዊ ንብረት ኮሚቴ ማቋቋሙንና ዘርፉን የሚመለከቱ ስራዎችን ለማከናወን እየሰራ መሆኑን ለተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡

## ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እድሎችና ተግዳሮቶች ላይ የአንድ ቀን ዐውደ ጥናት ተካሄደ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ "ክሊኒካል ሌጋል ኤዱኬሽን ፐብሊክ ኢንተርስት ፕሮጀክት" ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ አዳራሽ ውስጥ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን በሚመለከት የአንድ ቀን አውደ ጥናት አካሂዷል፡፡
በአውደ ጥናቱ ላይ የማኅበሩ አመራሮች፣ ከጠቅላይ ዐ/ሕግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች፣ ከተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ክፍል መምህራኖችና ነፃ የሕግ ድጋፍ ማዕከል አስተባባሪዎች፣ የፌደራል እና የክልል ፍ/ቤቶች ተወካዮች፣ የመንግሥት ተከላካይ ጠበቆች ቢሮ ተወካዮች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሙያ ማኅበራት ተወካዮች፣ የተለያዩ የሚዲያ አካላት እና ሌሎችም ተሳታፊ በሆኑበት በዚሁ ዓውደ ጥናት የማኅበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የእንኳን ደህና መጣችሁና የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ፤ የቀድሞ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም በአወያይነት፤ እንዲሁም አቶ እንዳልካቸው ወርቁ ከጠቅላይ ዐ/ሕግ የሕግ ማርቀቅና ማስረፅ ዳይሬክቶሬት በሃሳብ ሰጭነት ተካፍለዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ‹‹ነፃ የሕግ ድጋፍ እና ተግዳሮቶች በፍትኃ ብሔር ጉዳዮች›› እና ‹‹የተከላካይ ጠበቆች በኢትዮጵያ፡ ክፍተቶችና መፍትሔዎቻቸው›› በሚሉ ርዕሶች ሁለት ጥናታዊ ጽሑፎች በአቶ ጌትነት ምትኩና በአቶ አበራ ኃ/ማርያም እንደቅደምተከተላቸው ቀርበው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በውይይቱ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት በተለያዩ አካላት የሚሰጡ መሆናቸውና ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚስተዋሉባቸው መሆኑን፤ በተለይም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የሚለዩበት ወጥ የሆነ መስፈርት አለመኖሩ፣ የአገልግሎት ሰጪ አካላትም በቅንጅት አለመሥራታቸው፣ የአገልግሎት ጥራቱ እምብዛም መሆኑ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ በለጋሾች የገንዘብ ድጋፍ መኖር አለመኖር ላይ የተንጠለጠለ እና ቀጣይነቱ ሁልጊዜም አጠራጣሪ መሆኑ፣ የ50 ሰዓት ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ወሰኑ ምን ድረስ እንደሆነ በግልፅ አለመታወቁ እንዲሁም የተከላካይ ጠበቆች ቢሮ እራሱን ችሎ አለመቋቋሙ እራሱን የቻለ ተቋማዊ አደረጃጀትና መዋቅር የሌለው መሆኑና ሌሎች ተዛማጅ ችግሮች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

## ኢሕባማ የአዕምሯዊ ንብረትን በተለይም በርን (ስዊትዘርላንድ) እና ፓሪስ ኮንቬንሽን አንጻር የሚዳስሰ ውይይት አዘጋጀ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር(ኢሕባማ) "ዓለም አቀፍ ሥምምነቶች በአዕምሯዊ ንብረት በተለይ ከበርን (ስዊትዘርላንድ) እና ፓሪስ ኮንቬንሽን አንፃር" በሚል ርዕስ ላይ ቅዳሜ ሚያዝያ 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡30 - 6፡30 በግሎባል ሆቴል በመስኩ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው የሕግ ባለሙያዎች በአቶ አማን አሠፋ/በአ.አ.ዩ. የሕግ እና አስተዳደር ኮሌጅ መምህር፣ የሕግ አማካሪና ጠበቃ/ አቅራቢነት፣ እንዲሁም በአቶ ኤርሚያስ የማነብርሃን /በአዕምሯዊ ንብረት ኤጀንሲ የንግድ ምልክቶች ምዝገባና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር/ አወያይነት የግማሽ ቀን ትምህርታዊ ውይይት ማዘጋጀቱ ታወቀ፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ኢፌዲሪ የሳይንስ ሚኒስቴር ፤ለኢፌዲሪ የባሕል ሚኒስቴር የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር፤ የኮፒራይት የጋራ አስተዳደር ማኅበር ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ ፤የኦዲዮ ቪዥዋል አሳታሚዎች ማኅበር ፤የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ፤የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር ፤የኢትዮጵያ ፊልም ሠሪዎች ማኅበር በውይይቱ እንዲሳተፉ የተጋበዙ ሲሆን 46 የሚሆኑ ከሚመለከታቸው የመንግሰት እና መንግሰታዊ ያልሆኑ ባለ ድርሻ አካላት ከኢትዮጵያ የሕግ ባለለሙያወች ማኅበር አባላትና ሌሎች የሕግ

(ወደ ገፅ 5 የዞረ)

## በኢንሹራንስ ሕግ ላይ ውይይት ተደርገ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ሚያዝያ 14/2009 ዓ.ም.፣ ከጠዋቱ 2፡30 - 6፡30 በ"ኢንሹራንስ ሕግ" በተለይም በመድህን ሊሸፈን የሚችል ጥቅም (Insurable Interest)፤ የኃላፊነት ኢንሹራንስ እና ሠራተኛ እና አካል ላይ የሚደርስ ጉዳት ኢንሹራንስ ላይ ያተኮረ የግማሽ ቀን ትምህርታዊ ውይይት በዋቢ ሸበሌ ሆቴል አካሂዷል፡፡

ትምህርታዊ ውይይቱን በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የከፈቱት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የኢንሹራንስ ሕግ ሰፊ መሆኑን እና ውይይቱ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መሆኑንን በማስታወስ ለትምህርታዊ ውይይቱ መነሻ የሆኑትን ፅሁፎች ያቀረቡትን አቶ ይነበብ ደርሰህ -በኅብረት ኢንሹራንስ ሕግ አገልግሎት ሥራ አስኪያጅን፤ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ በሕግ መምህርነት ሲያገለግሉ የነበሩትና አሁን የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑትን አቶ ፋሲል አለማየሁን፤ እንዲሁም አወያዩን አቶ ቢንያም አህመድን እና አቶ ይነበብ ደርሰህን ለጊዜያቸው አመስግነው ውይይቱን ከፍተዋል፡፡ በዚህ ትምህርታዊ ውይይት ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ የመንግስትና የግል የመድን ድርጅቶች፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት፤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር አባላት እና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች የተጋበዙ ሲሆን 66 ተሳታፊዎች በውይይቱ ተካፍለዋል፡፡

# ቃለ-ምልልስ

## ከጠበቃ ማርቆስ ወልደሰንበት ጋር

**ጠያቂ፦የት እንደተወለዱ እና ያሳለፉትን የትምህርት ሂደት ቢነግሩን ?**

**አቶ ማርቆስ፦**የተወለድኩት በቀድሞ አጠራሩ ጨቦና ጉራጌ ተብሎ በሚጠራው በአሁኑ አጠራሩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጉራጌ ዞን ቸሀ ወረዳ ከአባቴ ከ አቶ ወልደሰንበት ሎቢቃ እና ከእናቴ ወ/ሮ አቴላች አረጋ በጋብቻ በ 1935 ተወልጃለው። ትምህርት የጀመርኩት በ 10 (አስር) አመቴ ነው። ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ የተማርኩት እንድብር ቀዳማዊ ሀይለስላሴ ት/ቤት ሲሆን የስምንት ዓመቱን ትምህርት በ ስድስት ዓመት ነው የጨረስኩት። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በጥሩ ውጤት አጠናቀኩ።

**ጠያቂ፦ወደ ሕግ ትህምርት እንዴት ሊገቡ እንደቻሉ ቢነግሩን?**

**አቶ ማርቆስ**፦ወደ ሕግ ሙያ የገባሁት በድንገት ነው። የገበሬ ልጅ እንደመሆኔ መጠን መማር የምፈልግ የነበረው ግብርና ነበር። የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትምህርት እንድማር ይመክሩኝ ነበር። ብዙ አስተማሪዎቼ ሜዲካል ስኩል (medical school) ለምን አትገባም ይሉኝ ነበር። አንዳንዶቹ ደግሞ ለምን ሎየር (lawyer) አትሆንም ይሉኝ ነበር። ሎየር የሚለውን ቋንቋ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ሰዓት ነበር ልሰማ የቻልኩት። እንዲህ ሊሉኝ የቻሉት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለን ትምህርት ቤቴን ወክዬ ዲቤቲንግ ሶሳይቲ (debating society) ውስጥ እሳተፍ ስለነበረ ነው። ፍላጎቴ የሕክምና ትምህርት መማር ቢሆንም ኢንጂነሪንግ ዲፓርትመንት ተመደብኩ። በዚህ መሀል አከቲቭ ፣ መሪ የመሆን እና ጥሩ ውጤት የማምጣት ፍላጎቴ ከፍተኛ ነበር። በ1956 ሚሊቴሪ አካዳሚ ገባው በአንዳንድ ምክንያት አቋረጥኩ። በቀጣዩ ዓመት ፐብሊክ ሄልዝ ኮሌጅ ገባው እሱንም ልገፋበት አልቻልኩም። ከዚህ በኃላ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። አንድ ማስታወቂያ አየሁ የሕግ ትህምርት መማር የምትፈልጉ የሚል። እኔም ለምን አልወዳደርም ብዬ ተወዳዳርኩ። በዛ ግዜ ወደ ሕግ ትምህርት ቤት ለመግባት ቢያንስ በማንኛውም የትምህርት አይነት አንድ ዓመት የኮሌጅ ትምህርት ማጠናቀቅና ከ 2.5 GPA በላይ ውጤት መያዝ ይጠበቅ ነበር። መስፈርቱን ስላላሟላሁ pre law program አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሕግ ት/ቤት መግባት ቻልኩ። ከዛ መማር ጀመርን። ልንጨርስ አንድ ዓመት ሲቀረን ማንኛውም የዩኒቨርስቲ ተማሪ ብሔራዊ አገልግሎት ማገልገል ግዴታው ስለነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት ተመድበን የዜግነት ግዴታችንን መወጣት ጀመርን። ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ተመድቤ ነበር ፍርድ አዘጋጅ ነበርኩ። ፕሬዚዳንቱ አቶ ንጉሴ ይባሉ ነበር። በደንብ አድርገው ነው የሞረዱኝ፤ ያሰለጠኑኝ። ከዚህ በኋላ አንድ ዓመት ስለቀረን ወደ ትምህርት ቤት ተመለስን። በዚህ ሰዓት ከፍርድ ሚኒስቴር ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን እንድንሰራ የቅጥር ጥያቄ ቀረበልኝ። ቅዳሜ ቅዳሜ በወቅቱ በነበረው የዲፕሎማ ደመወዝ ተቀጥረን መስራት ጀመርን። በ1963 ሰኔ ወር ላይ ከዩኒቨርስቲ ተመረቅን። ጥቅምት 1 ቀን 1964 ዓ.ም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኜ ተሾምኩ። የደርግ መንግስት መጣሁ መጣሁ ሲል እና ንቅናቄውም እየበረታ ሲመጣ ጃንሆይ ዘውዳዊ ስርዓት ለማድረግ በእንዳልካቸው ካቢኔ ሕገ መንግስት በሚረቀቀበት ወቅት በኤክስፐርትነት ተመድቤ አገለግል ነበር። በዛ ጊዜ የአሜሪካ መንግስት ለዳኞች የጉብኝት እድል ይሰጥ ነበርና እድሉ ደርሶኝ አሜሪካ ሄድኩ።

> ከዚህ አለም በሞት ከተለየሁ በኋላም እንኳን ስምህን ሊያስጠራ የሚችል ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ሠርቶ ማለፍ።

**ጠያቂ፦የህይወት ፍልስፍናዎ ምንድነው?**

**አቶ ማርቆስ፦** ከዚህ አለም በሞት ከተለየሁ በኋላም እንኳን ስምህን ሊያስጠራ የሚችል ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ሠርቶ ማለፍ።

**ጠያቂ፦አንድ ጠበቃ ብቁ ባለሙያ ለመሆን ምን ምን ማሟላት እና ማረጋገጥ አለበት ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ማርቆስ፦**እንደ እውነቱ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ መጀመሪያ ዲግሪ ካስተማርክ በኋላ ሁለተኛ ድግሪ እና ሶስተኛ ዲግሪ ሲማሩ ሥነ-ስርዓት ሕግ (ethical rule) ሊኖረው ይገባል። በዚህ ሰዓት የጠፋው ሥነ-ስርዓት ነው። ስለዚህ ሁሉም ቤተሰብ ልጁን ከስር ጀምሮ በሥርዓት ቢያሳድግ አሁን እያስተዋልን ያለነውን ችግር ባልተከሰተ ነበር። መማር እና ማንበብ ማንበብ።

**ጠያቂ፦ረቂቁ የንግድ ሕግ ሙያን በጋራ (Law firm) መልክ እንዲሰጥ ይፈቅዳል እርስዎ ይህንን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ማርቆስ**፦በኢትዮጵያ ውስጥ ሎው ፊርምን (law firm) ማን እንደከለከለ አይገባኝም። መንግስት ከለከለ ይላሉ። ሎው ፊርሙ ልዩ የሆነ አሶሴሽን ነው የሚሆነው እንጂ የንግድ ተቋም ሊሆን አይችልም። የሎው ፊርሙ መኖር ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት። ሎው ፊሪሙ ሥራ ሲጀምር

ስፔሻላይዜሽን ይፈጠራል። አብዛኞቻችን አጠቃላይ ሕግ ነው የተማርነው። የመጣልንን ጉዳይ ሁሉ እንቀበላለን። ሎው ፊርሙ ሲቋቋም ግን የሕግ ባለሙያ ምክር እና ድጋፍ ለሚፈልጉ ተገልጋዮች ከእውነተኛ ባለሙያዎች ጋር እንዲገናኙ ይረዳቸዋል።

ሌላ አገር ግን አጠቃላይ ትምህርት ከተማሩ በኋላ በተወሰነ ዘርፍ ስፔሻላይዝ ያደርጋሉ። ከሎፊርሙ ጥቅሞች ውስጥ ለባለሙያዎች ጉዳይ ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል፣ ተቋሙ ግብር ለመንግስት ይከፍላል እና መንግስት ከእያንዳንዱ ባለሙያ ገቢ ላይ ግብር ሊያስከፍል ይችላል።

**ጠያቂ፡-የነፃ የሕግ አገልግሎት** (Pro bono service) **አተገባበር ላይ ብዙዎች ጥያቄ እና ቅሬታ አላቸው እርስዎ በዚህ መርህ አተገባበር ላይ ያለዎት አስተያየት ምን ይመስላል?**

**አቶ ማርቆስ**፡-የሕግ ነጻ አገልግሎት በሚገባ ሥራ ላይ ውሏል ለማለት ይቸግራል። እንደ እኔ እሳቤ በፍርድ ቤት መዋቅር ውስጥ እራሱን የቻለ አስተዳደር ቢኖረውና ለጠበቆች ፍቃድ ከሚሰጠው አካል ጋር በቅንጅት ቢሰሩ ለተገልጋዮች አርኪና ተደራሽ አገልግሎት መስጠት ይቻላል ብዬ አምናለው። ይህ ደግሞ ለመጣው ጉዳይ የተገኘውን ጠበቃ ከመመደብ ይልቅ እንደ ሎው ፊርም በጉዳዩ ላይ ጠለቅ ያለ እውቀት ያለውን ባለሙያ ማግኘት ያስችላል።

**ጠያቂ፡-በእርስዎ እይታ ለአንባቢ ሶስት ምርጥ የሕግ መፃሕፍትን ጠቁሙ ቢባሉ እነማንን ይጠቁማሉ?**

**አቶ ማርቆስ**፡-ያነበብኳቸው መጽሀፍቶች ተዘርዝረው አያልቁም። አሁን ከማስታውሰው Justice,Civil action እና ሕንዶች የ ሲቪል ሕግ (civil law) የሕግ ስርዓት የሚከተሉ ስለሆኑ የእኛም ሀገር ሕግ ከዛም ስለተቀዳ እነሱ የጻፏቸውን መጽሀፍ አብዛኛውን ጊዜ አነባለው። በሌላ ጊዜ ዝርዝሩን ልሰጣቹ ቃል እገባለሁ።

**ጠያቂ፡- በመጨረሻ ለጠበቆች ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለዎት** ?

**አቶ ማርቆስ**፡-ከጠበቆች ማኅበር ብጀምር የጠበቆች ማኅበር ፍቃደኛ የሆነ ሰው ሁሉ ተጋብዞ መግባት አለበት። ከገባም በኋላ ማነው የሚመራኝ፣ እንዴት አድርጎ ነው የሚመራኝ፣ እና ከመንግስት ጋር እንዴት አግባብቶ ይመራናል ለሚለው የውስጡ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ማግኘት አለበት።ከዚህ በተጨማሪም ጠንካራና ተፈሪ መሆን አለበት። ለጠበቆች አጽንኦት ሰጥቼ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት ጥብቅና ማለት የተከበረ ሙያ ነው። ጠበቃም የተከበረ ባለሙያ ነው። ጠበቃ ማለት የጠብ እቃ አይደለም ጠባቂ እንጂ።ማንኛውም ጠበቃ የማያዋጣውን ጉዳይ ለገንዘብ ብሎ መያዝ የለበትም። ለማስታረቅ መጣር አለበት። እንደማያዋጣ እያወቀ ጉዳዮችን ቢይዝ ሁሌ መሸነፍ ይመጣል። ይህ ደግሞ ሌሎች ባለጉዳዮች ወደ እሱ እንዳይመጡ ያደርጋቸዋል። ጠበቃ በገለልተኝነት ዳኝነት መቀመጥ አለበት፤ ለገንዘብ ብሎ መሆን የለበትም።

## ኢሕባማ የጠበቆች የሥነምግባር ደንብ አፈፃፀም ተግዳሮቶችና ...

*(ከገፅ 1 የዞረ)*

የሚሰሩ መኖራቸውን አውስተው የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባዔ በተለያዩ ጊዜያት የሙያውን ሥነምግባር በመተላለፍ ከማስጠንቀቂያ እስከ ፈቃድ መንጠቅ ውሳኔ ያሳለፈባቸው ባለሙያዎች መኖራቸውን በመረጃ አስደግፈው ለተሳታፊው አቅርበዋል። በዳታ አስደግፈው ገልፀዋል። በውጭው ዓለም ጠበቆች እራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ሥርዓት መኖሩን የጠቆሙት አቶ አበበ በሀገራችን ግን የጥብቅናውን ሙያ ማኅበራት ሊያስተዳድሩ የሚችሉበት አቅም ላይ እንዳልሆኑ፤ መንግስትም ለዚህ ዝግጁ አለመሆኑን ጠቁመዋል።

ተሳታፊዎች በቀረቡት የመወያያ ፅሁፎች ላይ ጥያቄና አስተያየት የሰነዘሩ ሲሆን ከተሰነዝሩት ሃሳቦች የብዙዎችን ትኩርት የሳበው በአወያይ አቶ በሻዳ ገመቹ "እኛ ጠበቆች የሌሎችን ሰዎች ሕይወት፣ ሙብት እና ንብረት በአግባቡ እያስተዳደርን እንዴት የራሳችንን ጉዳይ ማስተዳደር ያቅተናል? የሚል ሞጋችና በሚል የጥብቅናው አስተዳደር በሕግ ባለሙያዎች ማኅበር አማካኝነት መምራት የሚችል ስለመሆኑ አመልካች አስተያየት መሰንዝራችው ታወቋል።

የማኅበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት ባደረጉት የመዝጊያ ንግግር ጽሁፍ አቅራቢዎች ጊዜያቸውን ሰውተው ፀሁፍ በማቅረባቸው እንዲሁም ኮርኳሪ ሃሰቦችን በመሰንዘራቸው ተሳታፊዎችም አስተያየትና ጥያቄዎችን በመሰንዘር በንቃት በመሳተፋቸው አመሰግነው ግቡን መቷል ብለዋል። አቶ ቴዎድሮስ ምህረት ችግሮቹ ዘላቂና ሀገራዊ መፍትሔ እስኪበጅላቸው ድረስ ወደፊትም ተከታታይ አውደጥናቶችና ውይይቶች መካሄድ እንዳለባቸው በመጠቆም ንግግራቸውን አጠቃለዋል።

## ኢሕባማ የአዕምሯዊ ንብረትን ...

*(ከገፅ 3 የዞረ)*

ባለሙያዎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች በአውደጥናቱ ላይ ተገኝተዋል።

የማኅበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በማድረግ የስብሰባውን በይፋ መከፈት ካበሰሩ በኋላ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከተለያዩ ባለድርሻ የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ በመፍጠር እና ሥነ-ሕግን በማሳደግ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል። የተከበሩ አቶ አባይነህ ተላከ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንዲሁም የማኅበሩን ጥሪ አክብረው በአውደጥናቱ ላይ ለተገኙ ባለሙያዎች ምስጋናቸውን አቅርበዋል። የስብሳበው ተሳታፊዎች በሚቀርበው ጽሁፍ ላይ ሃሳብ አስተያየታቸውን በመስጠትና እውቀትና ልምዳቸውን ያካፍላሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ለተሳታፊዎች የገለጹት የማህበሩ ፕሬዚዳንት የዕለቱን ትምህርታዊ ውይይት መድረክ ያዘጋጀው ማኅበሩ መሆኑን፤ አቶ አማን አሠፋ የመወያያ ጽሑፉን ከማቅረብ ባሻገር ለስብሰባው የሚያስፈልጉ ወጪዎችን በመሸፈን ስፖንሰር ያደረገ በመሆኑ ሊመሰገኑ እንደሚገባ' አመልክተው ከአእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ጊዜያቸውን ሰውተው አወያይ ለመሆን ፈቃደኛ በመሆን የመጡትን አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃንን እንዲሁም የማኅበሩን ጥሪ አክብረው በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ ባለሙያዎችን በማመስገን እና የዕለቱ ውይይት የተሳካ እንዲሆን በመመኘት የመክፈቻ ንግግራቸውን አብቅተዋል።

## በአዲሱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ውስጥ ስለተካተቱት አዳዲስ ድንጋጌዎች የቀረበ አጭር ማብራሪያ

በመስፍን ታፈሰና ጓዶቹ የሕግ ቢሮ

የንግድ ምዝገባ ማካሄድና የንግድ ፈቃድ ማውጣት በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም በንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው ማሟላት ያለበት ግዴታዎች ናቸው። እነዚህ ግዴታዎች ላለፉት ስድስት ዓመታት በንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 (**"የቀድሞው አዋጅ"**) መሰረት ሬጉሌት ሲደረጉ ነበር። ይህ የቀድሞው አዋጅ ተሽሮ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 (**"አዲሱ አዋጅ"**) ተተክቷል። አዲሱም አዋጅ ከሐምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም ስራ ላይ ውሏል። ይህንንም ተከትሎ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር 392/2009 (**'ደንብ'**) አውጥቶ ከመስከረም 4 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ ውሏል።

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በዚህ አዋጅና ደንብ ውስጥ የተካተቱትን አዳዲስ ለውጦችን እንደሚከተለው በአጭሩ እናቀርባለን።

### <u>የንግድ ምዝገባ ዓመታዊ እድሳት</u>

የንግድ ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት የሚያገኙት በምዝገባ ነው። የቀድሞው አዋጅ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በየዓመቱ ወይም በየአምስት ዓመቱ መታደስ እንዳለበት ይደነግግ ነበር። በየአምስት ዓመቱ የማሳደስ አማራጭ በንግድ ሚኒስቴር በኩል ተግባራዊ ያልተደረገ ሲሆን ሁሉም የንግድ ማህበራት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀታቸውን በየዓመቱ ሲያሳድሱ ቆይተዋል።

በአዲሱ አዋጅ ግን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በንግድ ምዝገባው ሰርተፊኬት ላይ የተገለፁት ሁኔታዎች ካልተለወጡ በስተቀር (<u>ለምሳሌ</u> አድራሻ) ሰርተፍኬቱ የማይለወጥና የማይታደስ አድርጎታል።

### <u>የፍራንቻይዝ ስምምነት</u>

በአዲሱ አዋጅ ውስጥ ከተካተቱት አዳዲስ ኃሳቦች መካከል የፍራንቻይዝ ስምምነት አንዱ ሲሆን በአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 2 (33) በተሰጠውም ትርጉም

> *እውቅና ባገኘው ምርት ወይም አገልግሎት ንግድ ስም ተጠቅሞ እውቅና ባገኘው ምርትና አገልግሎት ባለቤት መሪነት የስራውን ባህሪና ልምድ ለመካፈል በፍራንቻይዘርና በፍራንቻይዚ መካከል ለጥቅም ተብሎ የሚደረግ ስምምነት ነው።* ተብሏል

በአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 37 እና በደንቡ አንቀፅ 48 መሰረት የፍራንቻይዝ ስምምነት የሚመዘገብ ሲሆን ለዚህም ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። የፍራንቻይዝ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይታደሳል። ይህን ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለመውሰድና ለማደስ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች እንደቅደም ተከተላቸው በደንቡ አንቀፅ 49 እና አንቀፅ 50 ላይ ተደንግገዋል። የስራውን ጥራትና ደረጃ በተመለከተ ፍራንቻይዚው በፍራንቻይዘሩ ደረጃ መሰረት መስራት እንዳለበትና ተገልጋዮች ከፍራንቻይዘሩ የሚያገኙትን ዓይነት ምርት ወይም አገልግሎት ከፍራንቻይዚው ማግኘት እንዳለባቸው አዲሱ አዋጅ ይደነግጋል።

### <u>ሆልዲንግ ኩባንያ</u>

በንግድ ሕጉ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ሆልዲንግ ኩባንያ የተጠቀሰ ቢሆንም ድንጋጌዎቹ የተሟሉ ስላልሆኑ በእነዚህን ድንጋጌዎች መሰረት የሆልዲንግ ኩባንያን ትርጉም ለመስጠትና ለመመዝገብ አስቸግሮ ቆይቷል።

በአዲሱ አዋጅ ላይ ግን ሆልዲንግ ኩባንያ በአንቀፅ 2(40) ላይ እንደሚከተለው ትርጉም ተሰጥቶታል፤

> *ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ኃላፊነታቸው የተወሰኑ የንግድ ማህበራትን ያቀፈ ፣ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠውና በሆልደሩ የሚመራ ኩባንያ ነው።*

ሆልዲንግ ኩባንያ በሆልደሩ አማካይነት በንግድ ሚኒስቴር መመዝገብና የሆልዲንግ ኩባንያ ምዝገባ ልዩ የምስክር ወረቀት የማውጣት ግዴታ እንዳለበት አዲሱ አዋጅ (አንቀፅ 34) ይደነግጋል። የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይታደሳል። የሆልዲንግ ኩባንያውን ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣትና ለማደስ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው በደንቡ አንቀፅ 37 እና 38 ላይ ተደንግገዋል።

የሆልዲንግ ኩባንያው አባላት ከቡድኑ ሲወጡ ወይም ወደ ቡድኑ ሲቀላቀሉ ለመዝጋቢው አካል በማሳወቅ አስቀድሞ የተሰጠው ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት መለወጥ እንዳለበት አዲሱ አዋጅ የሚደነግግ ሲሆን፣ ሆልደሩ ኩባንያ ከሶስተኛ ወገኖች ለሚመነጩ ማናቸውም ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጥል ከቡድኑ ኩባንያ አባላት ጋር ኃላፊ እንደሆነ አዲሱ አዋጅ በተጨማሪ ይደነግጋል።

### <u>ስለብቸኛ አስመጪዎችና አከፋፋዮች</u>

አዲሱ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የንግድ ሚኒስቴር ለብቸኛ አስመጪዎችና አከፋፋዮች ፈቃድ አይሰጥም ነበር። አዲሱ አዋጅ ይህንን ሁኔታ በአንቀፅ 38 ላይ ግልፅ የሆነ የሕግ መሰረት ሰጥቶታል። ሆኖም ከሥራው ባሕሪ እና አገራዊ ጥቅም አንጻር ብቸኛ አስመጭ ወይም አከፋፋይ ሆኖ መሥራት የሚቻልባቸው የንግድ ሥራ መስኮችን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ እንደሚችል አንቀፁ በተጨማሪ ይደነግጋል።

### <u>የጠረፍ ንግድ</u>

አዲሱ አዋጅ ከዚህ በፊት በግልፅ የማይታወቅ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ አካትቷል። የጠረፍ ንግድ ማለት:

*“ ከኢትዮጵያ ድንበር አዋሳኝ በሆኑ ሀገሮች በሁለትዮሽ ስምምነት ወይም በተናጠል ውሳኔ በድንበር አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወይም ነጋዴዎች ሚኒስቴሩ በጠረፍ ንግድ መመሪያ በሚወስነው መሠረት ከሀገሪቱ ድንበር ባሻገር ጭምር በልዩ ሁኔታ የሚነግዱበት የንግድ ሥራ ዓይነት ነው።”*

የጠረፍ ንግድ ለማካሄድ ማንኛውም ሰው መመዝገብና የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ማውጣት አለበት። የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው በደንቡ አንቀፅ 42 እና 44 ላይ ተደንግገዋል።

**<u>የዘርፍ ማህበራትን ፤ የውጭ አገር ንግድ ምክር ቤቶችን እና ከውጭ አገር በኢንቨስትመንት የገቡ የሚያቋቁሙትን ማኅበር ስለመመዝገብ</u>**

በአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 6(3) መሰረት በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የዘርፍ ማህበራትና በንግድ ሚኒስትሩ ታምኖበት የተፈቀደላቸው የውጭ አገር ንግድ ም/ቤቶች ቅ/ፅ/ቤቶች በንግድ ሚኒስቴር እንደሚመዘገቡ ደንግጓል። የውጭ አገር ንግድ ም/ቤቶች ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ማከናወን የሚችሉት ተግባር በሀገር ውስጥ ያሉ የንግድና ዘርፍ ምክር ቤቶች ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጋር ተመሳሳይ ተግባራትን ብቻ እንደሆነ አዲሱ አዋጅ የሚያስረዳ ሲሆን ፤ የቅርንጫፍ ንግድ ምክር ቤቶቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ማሟላት ያለባቸው መረጃዎች በደንቡ አንቀፅ 17 ስር ተዘርዝረዋል።

ከዚህ ሌላ ከውጭ አገር በኢንቨስትመንት የገቡ ኢንቬስተሮች የራሳቸውን ማኅበር ሲያቋቁሙ በአገር አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንትን ለማስተዳደር በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል እንደሚመዘገቡ የአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 40(1) ያስረዳል። በዚህ መሰረት ከውጭ አገር በኢንቨስትመንት የገቡ የራሳቸውን ማኅበር ሲያቋቁሙ የሚመዘግባቸው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ይሆናል ማለት ነው።

**<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ የማውጫ ጊዜ</u>**

በቀድሞው አዋጅ ውስጥ ያልነበረ ከምዝገባ በኋላ ንግድ ፈቃድ መውጣት ያለበትን ጊዜ የሚወስን ድንጋጌ በአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 11 ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። በዚህም መሰረት ነጋዴው በንግድ መዝገብ ተመዝግቦ የንግድ ፈቃድ ሳያወጣ ለአንድ ዓመት የቆየ እንደሆነ መዝጋቢው መስሪያ ቤት የንግድ ምዝገባውን ሊሰርዝ እንደሚችል ይደነግጋል። ሆኖም የተመዘገበው ሰው በማምረት ወይም በኢንጂነሪንግ ወይም በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ንግድ ስራዎች ላይ የተሰማራ ከሆነ የኢንቨስትመንት ስራዎቹን ያላጠናቀቀበትንና የንግድ ስራ ፈቃድ ሊያወጣበት ያልቻለበትን በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ በየሁለት ዓመቱ በንግድ ስራ ፈቃድ ማሳደሻ ጊዜ ውስጥ እየቀረበ ሲጠይቅና ሲፈቀድለት ብቻ ምዝገባው ሳይሰረዝ እንዲቆይ ሊደረግ እንደሚችል ድንጋጌው በተጨማሪ ያስረዳል።

መዝጋቢው መስሪያ ቤት የንግድ ምዝገባ ስረዛ ከማድረጉ በፊት ግን ነጋዴው መቃወሚያ ሀሳብ ካለው እንዲያቀርብ በተመዘገበበት አድራሻ በደብዳቤ ሊያሳውቀው እንደሚገባ የአዲሱ አዋጅ ድንጋጌ ያስረዳል።

**<u>በአስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅሬታ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ</u>**

አዲሱ አዋጅ አንቀፅ 47 ላይ በአስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅሬታ የሚቀርብበትን አዲስ ስርዐት ዘርግቷል።በዚህም መሰረት አዋጁ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንብና መመሪያዎች በሚሸፍኗቸው በማናቸውም ጉዳዮች ላይ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን አግባብ ላለው ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል። የበላይ ኃላፊው አቤቱታውን ሰምቶ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ያላሳወቀ እንደሆነ ወይም ቅሬታ አቅራቢው የበላይ ኃላፊው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ከሆነ ቅሬታ አቅራቢው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል። አቤቱታውን ማቅረብ የሚችለው በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ ሲሆን የአቤቱታ ማቅረቢያም ጊዜም ውሳኔው ከተሠጠ ወይም ውሳኔው ለአቤቱታ አቅራቢው በፅሁፍ መድረስ ያለበት ጊዜ ካለፈ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ነው።

**<u>የግለሰብ ነጋዴ ወራሾች/ባለትዳሮች መብት</u>**

በቀድሞው አዋጅ መሰረት በትራንስፖርት ንግድ ሥራ ተሰማርቶ የነበረ ግለሰብ ነጋዴ ወራሾች እና/ወይም የትዳር ጓደኛ በንግድ ሥራው ለመቀጠል የንግድ ማኅበር ለማቋቋም ያልፈለጉ ከሆነ ከወራሾቹ አንዱ ወይም የትዳር ጓደኛው በሌሎቹ ወራሾች እና/ ወይም የትዳር ጓደኛው በሚሰጠው ውክልና መሰረት በንግድ መዝገብ ከተመዘገበ በኋላ በወኪሉ ስም የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሚሰጠው ደንግጎ የነበረ ሲሆን አዲሱ አዋጅ ይህንን በማስፋት በትራንስፖርት ንግድ ላይ ብቻ ተወስኖ የነበረውን መብት በማንኛውም ንግድ ስራ ላይ እንዲሆን አድርጎ

*(ወደ ገፅ 8 የዞረ)*

## ኢሕባማ ነፃ የሕግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን...

*(ከገፅ 1 የዞረ)*

ማግኘቱ የታወቀ ሲሆን በጋምቤላም ማኅበሩ ከክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙ ታውቋል።

ማኅበሩ በሁለቱም ከተሞች የሚገኙትን ነፃ የሕግ ድጋፍ ማዕከላትን የቢሮ እቃዎችን በማሟላት እና የሰው ኃይል በመመደብ ከዚህ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ አቅም ለሌላቸውና ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሕግ ምክርና የጽሑፍ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ሲታወቅ እነዚህን ማዕከላት ጨምሮ ኢሕባማ በአዳማ፣ በአሶሳ ፤ በጅግጅጋ እና በአዲስ አበባ ያቋቋማቸው ማዕከላት ብዛት ስድስት መድረሳቸው ከማኅበሩ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

## በአዲሱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ውስጥ ስለተካተቱት ...

*(ከገፅ 7 የዞረ)*

በአንቀፅ 24(3) ላይ ደንግጎታል።

**<u>አዳዲስ ቅጣት ድንጋጌዎች</u>**

<u>አንቀፅ 49(4)</u> የንግድ ሥራ ፍቃዱን እንዲጠቀምበት በሽያጭ፣ በኪራይ፣ በስጦታ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ ማንኛውም ነጋዴ ከብር ፶ሺ (ሃምሳ ሺ) እስከ ብር ፻ሺ (አንድ መቶ ሺ) የገንዘብ መቀጮ እና ከ፭ (አምስት) ዓመት እስከ ፲ (አሥር) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት የሚቀጣ ሲሆን አሳልፎ የሰጠው ለውጭ አገር ዜጋ በሆነ ጊዜ ከብር ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺ) እስከ ብር ፫፻ሺ (ሦስት መቶ ሺ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከ፯ (ሰባት) ዓመት እስከ ፲፭ (አሥራ አምስት) ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

<u>አንቀፅ 49(5)</u> የንግድ ሥራ አድራሻ ለውጥ በአዋጁ መሠረት በወጣው ደንብ በተመለከተዉ የጊዜ ወሰን ውስጥ ለመዝጋቢው መስሪያ ቤት ያላስታወቀ ማንኛውም ነጋዴ ከብር ፭ሺ (አምስት ሺህ) እስከ ብር ፲ሺ (አስር ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና እስከ ሦስት ወር በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

<u>አንቀፅ 49(6)</u> በንግድ መዝገቡ ላይ ማሻሻያ ሊያስከትል የሚችል ለውጥ አድርጎ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት በ ፴ ቀናት ውስጥ ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት ያላስታወቀ ማንኛውም ነጋዴ ከብር ፭ሺ (አምስት ሺህ) እስከ ብር ፲ሺ (አስር ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

**<u>ሌሎች</u>**

በቀድሞው አዋጅ አንቀፅ 11(4) ላይ አክሲዮን ማኅበር ያልሆነ የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ ሲያካሂድ የማህበሩ የገንዘብ መዋጮ ካፒታል በባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ መዝጋቢው ለባንኩ ደብዳቤ ይፅፍ ነበር። በአዲሱ አዋጅ ላይ በዝግ ሂሳብ የማስቀመጥ አሰራር ቀሪ ሆኗል።

የቀድሞው አዋጅ ከሚመለከተው ሴክተር መ/ቤት የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከንግድ ፈቃድ ጋር በየዓመቱ እንዲታደስ የሚጠይቅ የነበረ ሲሆን፣ በአዲሱ አዋጅ ግን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሚጠየቀው ነጋዴው በሚመዘገብበት ጊዜ ብቻ ሆኖ የንግድ ፈቃድ ሲታደስ ይጠየቅ የነበረው የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ቀሪ እንዲሆን ተደርጓል።

ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረውና በቀድሞው አዋጅ ቀሪ እንዲሆን ተደርጎ የነበረው የንግድ ማህበራት ሲቋቋሙ በጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ የማድረግ አሰራር በአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 7(2) ስር እንደገና እንዲካተት ተደርጓል። በዚህም መሰረት አዋጁ ስራ ላይ ከዋለ ጀምሮ የሚቋቋሙ የንግድ ማህበራት የሀገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ መደረግ ይኖርባቸዋል።

የቀድሞው አዋጅ የአክሲዮን ማኅበር ሥራ አስኪያጅ የሌላ የንግድ ማኅበር ሥራ አስኪያጅ እንዲሆን አይፈቀድለትም ነበር። አዲሱ አዋጅ በአንቀፅ 41 ላይ ይህንን ሁኔታ በማስፋት የንግድ ማኅበር ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ ወቅት ከአንድ በላይ የንግድ ማኅበር ስራ አስኪያጅ መሆን እንደማይችል ደንግጓል።

## ከሐምሌ 2008 - ሰኔ 2009 ዓ.ም የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያዎች ማኅበርን የተቀላቀሉ አዳዲስ አባላት እና ተባባሪ አባላት ስም ዝርዝር

1 መስዑድ ገበየሁ
2 ቁምላቸዉ ባልቻ
3 መሳይ ተድላ
4 ወንድሙ ኢብሳ
5 ልደቱ አየለ
6 ያሬድ አለማየሁ
7 ሄኖክ ጫላ
8 መአዛ ወንድሜነህ
9 ሙሉጌታ ጉግሳ
10 አብዱርህማን መሀመድ
11 አዲሱ ድሬሳ
12 የኃለሽት ታምሩ /ተባባሪ አባል/
13 አበራ አንጃአቦ
14 ታየ አስራት
15 ኢርብ አለሙ
16 ደረሰ ሱራፌል
17 ኢምሩ ረዳ
18 ይነበብ ደርሰህ
19 ፋሲል አለማሁ
20 ሽፈራዉ ጉሌ
21 ኤሚ ደረሰ
22 ሲሳይ ወርቅነህ
23 ትንሳኤ ሰይፈ
24 ያሬድ ኃ/ማርያም
25 ዘንባባዉ ዘመድኩን
26 ኡስማን መኮንን /ተባባሪ አባል/
27 ጋሻዉ ተገኝ
28 ወሰንየለህ ጥጉ
29 ካሣሁን ወርቁ
30 ሙሉቀን ተሾመ
31 ቢንያም ታፈሰ

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሞያዎች ማኅበር
ሰኔ 30 ቀን 2009ዓ.ም. ቅፅ ፩ ፤ ቁጥር ፩

## <u>የሐዘን መግለጫ</u>

### በ2008/2009 ዓ.ም በሞት የተለዩ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ስም ዝርዝር

- አቶ ብርሃነመስቀል ወ/ጻድቅ
- አቶ ቀፀላ ሙላት
- አቶ አሸናፊ ረጋሳ
- አቶ በለው አብዲ
- አቶ አስቻለው ስጦታው ማርዬ
- አቶ ተሾመ ገብረማርያም ቦኮን
- አቶ ጌታቸው ደስታ

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሞያዎች ማኅበር

ሥልክ፡
+251-011-553-0122

ፋክስ፡
251-011-515-2047

መ.ሣ.ቁ.፡
700

ኢ-ሜይል፡
eba@ethionet.et

ድረገፅ፡
www.ethiopian-bar.org